አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

አንደኛ ዓመት ቁጥር ፳
አዲስ አበባ ፪ሺህ፪ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

1st year No. 20
ADDIS ABABA 2009

<u>ማውጫ</u>

<u>አዋጅ ቁጥር ፳/፪ሺ፪ ዓ.ም.</u>

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ.........................ገጽ ፩

**CONTENT**

**<u>Proclamation No. 20/2009</u>**

**A Proclamation to Establish the Mass Media Agency of Addis Ababa City Government.............. Page 1**

<u>አዋጅ ቁጥር ፳/፪ሺ፪ ዓ.ም.</u>

<u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር</u>

<u>መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ</u>

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግሥት በተደነገገው መሠረት የአሰራር ነፃነት ኖሮት የተለያዩ አመለካከቶችን በሚያስተናግድ መንገድ እንዲደራጅ ማድረግ በማስፈለጉ፤

ኤደንሲው ወቅታዊ መረጃዎችን ለህዝቡ በማቅረብ ረገድ ብቁና ተወዳዳሪ ተቋም ሆኖ እንዲወጣ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የኤደንሲው መቋቋም በከተማው አስተዳደር ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚኖረው አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑ ስለታመነበት፤

የከተማው አስተዳደር የከተማውን ነዋሪ የልማቱ ተጠቃሚ ለማድረግና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ እየተገበረ በመሆኑና ይህንንም ለመደገፍ ጠንካራ የመገናኛ ብዙሃን ተቋም በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት በተሻሻለው የከተማው አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ ዓ.ም. አንቀጽ ፲፬/፩/ረ/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

**<u>Proclamation No. 20/2009</u>**

***<u>A Proclamation to Establish the Mass Media Agency of Addis Ababa City Government</u>***

WHEREAS, it is found necessary to organize the Addis Ababa City Government Mass Media Agency independently and in a way to accommodate different views as provided in the Constitution of the Federal Democratic Republic Ethiopia;

WHEREAS, it is found necessary to come up with an Agency which is effective and competent as regards providing up-to-date information to the public;

WHEREAS, it is believed that establishing the Agency is of greatest contribution towards the economic, political and social development activities of the City Government.

WHEREAS, the City Government is currently implementing the business process reengineering with the view to make the residents of the City beneficiary of the development activities and the existence of strong mass media institution is found necessary in order to support this activity;

NOW THEREFORE, in accordance with Article 14(1)(f) of the Revised Charter Proclamation No. 361/2003 of the Addis Ababa City Government, it is proclaimed as follows:

አዲስ ነጋሪ ጋዜታ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 4.95

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ ለቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር ፳/፪ሺ፪ ዓ.ም.›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩. ‹‹መገናኛ ብዙሃን›› ማለት በየጊዜው በሚወጡ ህትመቶችና የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎቶች አማካኝነት ልዩ ልዩ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማዘጋጀትና በማሰራጨት ሥራ ላይ የተሰማሩ ተቋማት ናቸው፡፡

፪. ‹‹ጋዜጠኛ›› ማለት በሪፖርተርነት በኤዲተርነት፣ በአዘጋጅነት፣ በሰአሊነት፣ በፎቶግራፍ አንሺነት፣ በቪዲዮ ምስል ቀራጭነትና አቀነባባሪነት፣ በፊልም ዳይሬክተርነት፣ በፕሮዳክሽን ቴክኒሻንነት ወይም በጠቅላላው ለህዝብ የሚሰራጭ ልዩ ልዩ ዘገባዎች በማዘጋጀት ላይ ያተሰማራ የኤጀንሲው ሠራተኛ ነው፡፡

፫. ‹‹መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ›› ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ መሠረት የሚቋቋም ነጻ አካል ነው፡፡

፬. ‹‹ድጋፍ ሰጭ›› ማለት በኤጀንሲው ውስጥ በድጋፍ ሰጭ የሥራ ክፍሎች ማለትም በሰው ኃይል አስተዳደር፣ በፋይናንስ፣ በንብረት አስተዳደር እንዲሁም በኦዲት መስክ እና በመሳሰሉት የሚሠራ ሠራተኛ ነው፡፡

፭. ‹‹ሰው›› ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ነው፡፡

፮. ‹‹ቦርድ›› ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ መሠረት የተቋቋመ የመገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ ሥራ አመራር ቦርድ ነው፡፡

፯. ‹‹ሚዲያ›› ማለት ኤጀንሲው ዜና እና ዜና ነክ መረጃዎችን ለማሰራጨት የሚያቋቁማቸው የሬዲዮ፣ የቴሌቪዝን፣ የህትመት ወይም የድረገጽ መገናኛ ብዙሃን ነው፡፡

፰. ‹‹ማስታወቂያ›› ማለት በአገልግሎት ክፍያ ወይም እንደአስፈላጊነቱ በነፃ በመገናኛ ብዙሃን ወይም በባለማስታወቂያው ወይም ባለማስታወቂያው በሚያሠራው ሌላ አካል ተዘጋጅቶ ለህዝብ በኤጀንሲው የህትመት ውጤቶች ወይም በኤሌክሮኒክስ ሚዲያዎች የሚሰራጭ የምርትና የአገልግሎት ማስተዋወቂያ፣ የስብሰባ ጥሪ ወይም ትምህርታዊ መልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴ ነው፡፡

፱. ‹‹ምክር ቤት›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ነው፡፡

## *Part one*

## *General provision*

### *1. Short Title*

This proclamation may be cited as the "Addis Ababa City Government mass Media Agency Establishment Proclamation No. 20/2009"

### *2. Definitions*

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:-

1) "Mass Media" means an institution engaged in the activity of collecting, producing and broadcasting different information through periodical publications and electronic services.
2) "Journalist" means an employee of the Agency who is engaged in reporting, editing producing, painting, photography, taking video and organizing the same, directing film, working as technician of production or generally engaged in different reports that are to be broadcasted to the public.
3) "Mass Media Agency" means an independent organ established in accordance with Article 4/1/ of this Proclamation.
4) "Support staff" means an employee of the Agency engaged in supportive activities like human resource management, purchasing, finance, and resource administration, and auditing.
5) "Person" means natural or legal person.
6) "Board" means the management board of the Agency established in accordance with Article 9 of this Proclamation.
7) "Media" means radio, television, publication or website mass media established by the Agency to broadcast news and news related information.
8) "Advertisement" means a method of promoting goods and service, announcing meeting call or transmission of educational message prepared by mass media or the owner of the advertisement or a third person working for the owner of the advertisement and broadcasted to the public through the Agency's publications or electronic media, up on payment or free of charge, as the case may be.
9) "Council" means the Addis Ababa City Government Council.

፫. የፆታ አገላለጽ

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## ክፍል ሁለት

## መቋቋም፣ ዓላማና አደረጃጀት

፬. መቋቋም

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ ከዚህ በኋላ ‹‹ኤጀንሲ›› እየተባለ የሚጠራ ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ይሆናል፡፡

፭. ዋና መስሪያ ቤት

፩. የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ከተማ በማዕከል ይሆናል፡፡

፪. ኤጀንሲው እንደአስፈላጊነቱ በክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤት ወይም ከአዲስ አበባ ውጭ ወኪል ሊኖረው ይችላል፡፡

፮. ዓላማ

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. ለከተማ አስተዳደሩ ህዝብ ወቅታዊ እና ትክክለኛ መረጃዎችን በማሰራጨት በህዝቡና በከተማው አስተዳደር አመራር መካከል የጋራ መግባባት እንዲፈጠር መሥራት፤

፪. በዋና ዋና አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠር የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት፤

፫. በፌደራል ወይም በከተማ አስተዳደሩ ህጎች መሠረት የህዝቡን ሐሳብ በነፃ የመግለጽና የማንሸራሸር ነፃነትን ማበረታታት፤

፬. በከተማ አስተዳደር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንዲሁም የመልካም አስተዳደር ግንባታ ጥረት ውስጥ አጋዥ ሚና መጫወት፤

፭. በከተማ አስተዳደሩ መካከል እንዲሁም በመላ አገሪቱ እያደገ የመጣው የዲሞክራሲ ባህል ይበልጥ እንዲጐለብት ማበረታታት፤

፯. የኤጀንሲው አደረጃጀት

ኤጀንሲው የሚከተሉት የሥልጣን አካላት ይኖሩታል፡-

፩. የሥራ አመራር ቦርድ

፪. ዋና ዳይሬክተር

፫. ምክትል ዳይሬክተር

፬. ሌሎች አስፈላጊ የሥራ ክፍሎች

፰. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

ኤጀንሲው፡-

፩. ለከተማው ነዋሪ ጠቀሜታ ያላቸውን ዜና እና ዜና ነክ መረጃዎችን፣ ፕሮግራሞችን፣ መግለጫዎችንና ትንታኔዎችን እያዘጋጀ ያሰራጫል፤

***3. Gender Reference***

The provision of this proclamation, unless the context requires otherwise, set out in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

## *Part Two*

## *Establishment, Objective and Organizational Structure*

***4. Establishment***

1) The Addis Ababa City Government Mass Media Agency, hereinafter referred to as "the Agency" is hereby established being independent entity with its own legal personality.

2) The Agency shall be accountable to the Council of the Addis Ababa City Government.

***5. Head Office***

1) The head office of the Agency shall be in Addis Ababa at central level.

2) The Agency may have, where necessary, office at sub city level within Addis Ababa or correspondents outside Addis Ababa.

***6. Objective***

The Agency shall have the following objectives:-

1) to work towards creating common understanding between the City Government officials and the residents by transmitting accurate and current information.

2) to provide its own contribution towards creating national consensus on major national issues.

3) to encourage the public to express and exercise freely its freedom of thought in accordance with the laws of the Federal Government and Addis Ababa City Government.

4) to play supportive role in the economic, social as well as good governance building efforts of the City Government.

5) to encourage further strengthening of the democratic culture, which is already growing up within the City and at national level.

***7. Organizational Structure***

The Agency shall have the following organs:

1. Management Board,
2. General Director,
3. Deputy Director, and
4. Other departments necessary.

***8. Power and Function of the Agency***

The Agency shall:-

1) Prepare and disseminate news and news related information, programs, press release and analysis which are beneficial to the residents of the City.

፪. የኤሌክትሮኒክስ የህትመት ሚዲያዎችን ያቋቁማል፣ ያደራጃል፣ ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂና ቀልጣፋ አሠራር የሚጠናከሩበትን ስልት እያጠና ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫. የመንግሥትን አጠቃላይ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ህጎች ያስተዋውቃል የከተማው ነዋሪም በነዚህ ላይ አስተያየቱን የሚሰጥባቸውንና የሚወያዩባቸውን መድረኮች ያመቻቻል፤

፬. የከተማው ነዋሪ ህዝብ ስለአገሪቱ ህገ መንግሥት፣ ስለ ከተማው አስተዳደር ቻርተር፣ ሌሎች ህጎችና በተለይም ስለሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለውን ግንዛቤ ለማጐልበት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

፭. የህዝቡን ጠቅላላ እውቀት የሚያዳብሩ አዝናኝ ዝግጅቶችን ያቀርባል፤

፮. የአዲስ አበባ ከተማን ባህላዊ፣ ታሪካዊና ተፈጥሮአዊ ሀብቶችና እሴቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያስተዋውቃል፤

፯. የከተማ አስተዳደሩን ወቅታዊ የልማት፣ የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች፣ ክንውኖችና አጀንዳዎችን ተከታትሎ ይዘግባል፤

፰. የፎቶግራፍ፣ የማስታወቂያ፣ የዶክመንቴሽን እና ሌሎች የዶክመንተሪ ፕሮግራም አገልግሎቶችን ለደንበኛው በተመጣጣኝ ክፍያ ይሰጣል፤

፱. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፰ ድንጋጌ ቢኖርም ቦርዱ በሚያወጣለት መመሪያ መሠረት የማስታወቂያ አገልግሎት ከክፍያ ነፃ ይሰጣል፤

፲. በአገሪቱ ህጐችና ደንቦች መሠረት ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር ተመሳሳይ የመገናኛ ብዙሃን አካላት ወይም ድጋፍ ሰጭዎች ጋር መረጃ ለመለዋወጥ፣ የልምድ ልውውጥ ለማድረግና የሥልጠና እና የቴክኒክ ድጋፍ ለማግኘት ግንኙነቶችን ይመሠርታል፤

፲፩. በክፍያ የሚሰጡ የአገልግሎት ዓይነቶችና ተገልጋዮችን ይለያል፤ የአገልግሎት ዋጋ ተመን አጥንቶ በቦርዱ እንዲፀድቅ ያቀርባል፤

፲፪. አጠቃላይ መዋቅሩንና የሰው ኃይል በተመለከተ ጥናት ያደርጋል፣ እንዲፀድቅም ለቦርዱ ያቀርባል፣ የሥራውን ልዩ ባህሪ በመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ ያለውን የገበያ ተፎካካሪነት፣ የከተማ አስተዳደሩን የመክፈል አቅም ከግምት ባስገባ መልኩ የኤጀንሲውን ጋዜጠኞችና ሌሎች ሠራተኞች ደመወዝ፣ ጥቅማጥቅም ያጠናል፣ ለቦርዱም ያቀርባል፣ ያስፀድቃል፤

፲፫. የሠራተኛ አስተዳደር ማኑዋል አጥንቶ ለቦርድ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፬. የፋይናንስ የግዥና ንብረት አስተዳደር ማኑዋል ያጠናል፣ ለቦርዱም አቅርቦ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣

2) Establish and organize electronics and publication media and conduct a study and implement strategies that help strengthen the same with modern technology, competent professionals and effective performance;

3) Promote the general policies, strategies and laws of the Government and facilitate forums for the public to deliberate on and give opinion on them;

4) Work in collaboration with other stakeholders towards enhancing awareness of the residents of the City, other laws and specially human and democratic rights;

5) Provide recreational programs which develop the General knowledge of the public;

6) Promote the Addis Ababa City's cultural, historical and natural resources and values in collaboration with concerned bodies;

7) Timely report the achievements of the City Government as regards development, democracy and good governance issues, performances and agendas;

8) Render photography, advertisement, documentation and other documentary program services to customers at reasonable charge.

9) Notwithstanding the provisions of sub-article 8 of this Article, render advertisement service free of charge in accordance with the directive to be issued by the Board.;

10) Establish relations with counterpart local and international mass media agencies, with the view of sharing experience and information and obtaining technical assistance in accordance with the laws and regulations of the country;

11) Identify types of services to be rendered with charge; conduct study on costs of service and submit the same to the Board for approval;

12) Conduct study as regards the organizational structure and human resource of the Agency and submit the same to the Board for approval; conduct study and submit for approval to the board the benefit and salary scheme of the journalists and other civil service of the Agency by taking into account the special character of the job, capacity of the City Government to pay, the market competition in the field of mass media;

13) Conduct study and submit to the Board for approval the personnel manual of the Agency and implement the same upon approval;

14) Conduct study and submit to the Board for approval the finance, purchasing and resource management manual and implement the same upon approval;

፲፭. ከቦርዱ የሚሰጡትን መመሪያዎች ሥራ ላይ ያውላል።

፲፮. ዓላማውን ለማሳካት የሚያስችሉትን ሌሎች ህጋዊ ተግባራትን ያከናውናል።

## ፱. የቦርዱ አወቃቀርና ተጠሪነት

፩. የቦርዱ አባላት ፲፩ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ፲፫ ይሆናሉ።

፪. የቦርዱ ሰብሳቢ በከንቲባው አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይሰየማል።

፫. የቦርዱ አባላት አግባብነት ካላቸው የከተማ አስተዳደሩ የመንግሥት አካላትና የህብረተሰብ ክፍሎች ተውጣጥተው በከተማው ከንቲባ አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይሰየማሉ።

፬. የቦርዱ ተጠሪነት ለከተማው ምክር ቤት ይሆናል።

## ፲. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ፡-

፩. ኤጀንሲው የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር በአግባቡ መወጣቱን ያረጋግጣል፤

፪. ኤጀንሲው ለከተማ አስተዳደሩ ህዝብ በየወቅቱ የመንግሥት መረጃዎችን በስሩ ባደራጃቸው ልዩ ልዩ መገናኛ ብዙሃን አማካኝነት በብቃት ማስተላለፉን ይከታተላል፤

፫. ኤጀንሲው የመንግሥት ፖሊሲዎችን፣ አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ለህዝቡ በተገቢ መንገድ ማስተዋወቁን ያረጋግጣል፤

፬. በኤጀንሲው ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን ይመረምራል፤

፭. የኤጀንሲውን የመረጃ አሰጣጥ ሚዛናዊነት ይከታተላል፤ ስህተቶች ሲያጋጥሙ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

፮. የኤጀንሲው ተቋማዊ ብቃትና አገልግሎት አሰጣጥ በየጊዜው የሚሻሻልበትንና የሚጠነክርበትን አቅጣጫዎች ይቀይሳል፤ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፤

፯. በኤጀንሲው ተጠንቶ የቀረበለትን የዋጋ ተመን ያፀድቃል በክፍያና ከክፍያ ውጭ የሚሰጡ አገልግሎቶችን አይነቶችና ተገልጋዮችን በሚመለከት ይወስናል፤ የአገልግሎት ዋጋ ተመን ተጠንቶ እንዲቀርብለት በማድረግ ያፀድቃል

፰. የኤጀንሲውን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ህግ መሠረት መቀጠራቸውን ያረጋግጣል፣ የጋዜጠኞችን ደመወዝና ጥቅማጥቅም ያስጠናል፣ ይወስናል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ያሻሽላል፤

፱. በኤጀንሲው ተጠንቶ የቀረበውን የአስተዳደር ሠራተኞች ማኑዋል ያፀድቃል፤

፲. የፋይናንስ የግዥና የንብረት አስተዳደር ማኑዋል አግባብነት ያላቸው ህጎች ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ለአሰራርና ቅልጥፍና በሚያመች መልኩ በጀደንሲው እንዲጠናና እንዲቀርብለት በማድረግ ያፀድቃል፣ ተግባራዊ መሆኑን ይቆጣጠራል፤

15) Implement directives given to it by the Board.

16) Carryout other lawful activities enabling it achieve its objectives.

## 9. *Organization and Accountability of the Board*

1) The number of members of the Board shall be 11 or, where necessary 13.

2) The chairperson of the Board shall be nominated by the City Council up on recommendation of the Mayor.

3) Members of the Board shall be nominated by the City Council upon recommendation of the mayor being drawn from different appropriate public organs of the City Government and parts of the society.

4) The Board shall be accountable to the City Council.

## 10. *Power and function of the board*

The board shall:-

1. Ensure that the Agency properly discharge its function and responsibility.
2. Follow up that the Agency efficiently transmits current information to the residents of Addis Ababa City through different mass media it establish.
3. Ensure that the Agency properly promotes to the public policies, proclamations, regulations and directives of the Government.
4. Investigate into and pass decision up on grievance raised against the Agency by gathering public opinion.
5. Follow up that the Agency disseminates balanced information; take corrective measures where mistake occurs.
6. Design directions whereby the institutional capacity and service delivery of the Agency will be improved and strengthened from time to time, follow up implementation of the same.
7. Approve the service fee submitted by the Agency, pass decision regarding the type of service to be rendered with or without payment of service charge and beneficiaries of such service.
8. Ensure that the support staff of the Agency are employed in accordance with the civil service law; cause the salary and benefit scheme of journalists studied, fix and, where necessary, improve the same.
9. Approve the civil service personnel manual studied and submitted to it by the Agency.
10. Notwithstanding the provisions of other relevant laws, approve finance, purchase and resource management manual of the Agency by causing the Agency conduct a study of the same in a way that it is comfortable and facilitating the job.

፲፩. የኤጀንሲው የአጭርና የረጅም ጊዜ የመደበኛና ካፒታል በጀት እንዲሁም የሥራ እቅድ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብለት በማድረግ እንዲሁም ስለአፈፃፀሙ ሪፖርት አስቀርቦ በማየት ያፀድቃል፣ በአፈፃፀም አቅጣጫዎች ላይ ውሣኔ ይሰጣል፤

፲፪. ኤጀንሲው ከአስተዳደሩ የሚመደብለትን፣ ከውስጥ ገቢው፣ ከእርዳታ፣ የሚያገኘውን ገንዘብ ባግባቡ ለታለመለት ተግባር ማዋሉ ይቆጣጠራል፣ በአፈፃፀም ችግሮች ላይ ውሣኔ ይሰጣል፤

፲፫. በዋና ዳይሬክተሩ አቅራቢነት የኤጀንሲውን ምክትል ዳይሬክተር ይሾማል፣ የኤጀንሲውን ሌሎች ከፍተኛ የአመራር አካላት አመላመልና የሥራ ምደባ ይወስናል፣ እንደአስፈላጊነቱ የአፈፃፀም መመሪያ ያወጣል፤

፲፬. የኤጀንሲውን የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት በወቅቱ ለከተማው አስተዳደር ምክር ቤት ያቀርባል።

## ፲፩. የቦርዱ ስብሰባና ተጠያቂነት

፩. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም የቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ከቦርዱ አባላት አንድ ሦስተኛው ከጠየቁ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤

፫. በስብሰባው ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፤

፬. ማንኛውም የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ላይ ከተገኙ አባላት በድምጽ ብልጫ ሆኖ ድምጹ እኩል ለእኩል ከሆነ የቦርዱ ሰብሳቢ የደገፈው ወገን ሃሳብ የቦርዱ ውሳኔ ይሆናል፤

፭. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፤

፮. ቦርዱ የኤጀንሲውን ምክትል ዳይሬክተር በቦርዱ ስብሰባ ያለድምጽ እንዲሳተፍ እና ቃለ-ጉባዔ ያዥና ፀሐፊ አድርጎ ይሰይማል።

## ፲፪. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩. ዋና ዳይሬክተሩ በከንቲባው ይሾማል፤

፪. ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኤጀንሲውን ሥራ በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ ኤጀንሲውን ያስተዳድራል፤

፫. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) የኤጀንሲውን ጽህፈት ቤት ያደራጃል፤

ለ) በቦርዱ ውሳኔና በሲቪል ሰርቪስ ህግ መሠረት የኤጀንሲውን ሰራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

11. Deliberate on and approve the short and long term recurrent and capital budget, work plan, as well as implementation reports of the Agency; pass decision on directions of execution.

12. Control that the Agency uses the internal income, the budget allocated by the City Government, and the money found from donation for the purpose sought; pass decision on problems of execution.

13. Appoint the deputy director of the Agency upon recommendation of the General Director and decide on the recruitment and deployment of other higher management organs; issue, where necessary, directives of execution.

14. Submit timely report of the Agency to the City Council.

## *11. Meeting of the Board and Liability*

1. The Board shall conduct regular meeting once in a month.
2. Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, emergency meeting shall take place where the chairperson, or one third of the Board members so request.
3. There shall be quorum where more than half of the members of the Board are present.
4. Decision of the Board shall be passed by majority vote of those present in the meeting; in case of a tie the chairperson shall have a casting vote.
5. Without prejudice to the provisions of this Article the Board may issue regulation on its meeting procedure.
6. Each member of the Board, who participated in the decision, shall be jointly and severally liable.
7. The Board shall nominate the deputy director as the secretary and minutes keeper, without the right to voting.

## *12. Power and Function of the General Director*

The General Director shall:-

1. be appointed by the Mayor.
2. direct, control and administer the Agency in accordance with the general direction given to him by the Board.
3. Without prejudice to the general provision of sub-article (2) of this Article, the General Director shall;
   a) Organize office of the agency,
   b) Employ, administer, and dismiss the employee of the Agency in accordance with the civil service law and decision of the Board,

ሐ) የኤጀንሲውን የአጭር ፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅዶች በማውጣት እንዲሁም በጀትን በማዘጋጀት ሲፀድቅለት ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) የኤጀንሲውን ሃብት በበላይነት ያስተዳድራል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ረ) የኤጀንሲውን የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት በየሩብ ዓመቱና በተጠየቀ ጊዜ እያዘጋጀ ለቦርዱ ያቀርባል፤

ሰ) ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

፬. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ስር የተዘረዘሩትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፤

**፲፫. የምክትል ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

፩. ምክትል ዳይሬክተሩ በዋና ዳይሬክተሩ አቅራቢነት በቦርዱ ይሾማል፡፡

፪. ምክትል ዳይሬክተሩ ተጠሪነቱ ለዋና ዳይሬክተሩ ይሆናል፡፡

፫. ከዋና ዳይሬክተሩ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በሥሩ የተመደቡለትን ዘርፎች ተግባራት ይመራል፣ ያስፈፅማል የአፈፃፀም ሪፖርት አዘጋጅቶ ለዋና ዳይሬክተሩ ያቀርባል፡፡

፬. የቦርዱን ስብሰባ ቃለጉባዔ ይይዛል፣ ያደራጃል፡፡

፭. ከዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**ክፍል ሦስት**
**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**፲፬. የበጀት ምንጭ**

የኤደንሲው የበጀት ምንጭ በከተማው አስተዳደር ከሚመደብለት በጀት፣ ከውስጥ ገቢና ከእርዳታ ይሆናል፡፡

**፲፭. የሂሳብ መዛግብት**

፩. ኤጀንሲው የተሟላና ትክክለኛ የሂሣብና የንብረት መዛግብት ይይዛል፡፡

፪. የኤጀንሲው ሂሳብ በከተማ አስተዳደሩ ዋና ኦዲተር ወይም እሱ በሚወክለው ኦዲት በየጊዜው ይመረመራል፡፡

**፲፮. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጐች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተካተቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፲፯. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**
**ህዳር ፩ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.**

**ኩማ ደመቅሳ**
**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

c) Prepare the short, medium and long-term plans as well as budget of the Agency; implement the same upon approval,

d) Superiorly administer resource of the Agency,

e) Represent the Agency in relations with third parties,

f) Prepare and submit quarterly report of the Agency or upon request to the Board,

g) Carry out other activities given to him by the Board.

4. Perform the power and function of the Agency as provided for in Article 8 of this proclamation.

***13. Power and Function of the Deputy Director***

1. The deputy director shall be appointed by the Board upon recommendation of the General Director.

2. The deputy director shall be accountable to the General Director.

3. The deputy director shall direct, execute, prepare and submit report to the General Director, in accordance with directives given to him by the General Director, as regards operation of the sectors assigned to him.

4. He shall perform other activities given to him by the General Director.

5. He shall perform other activities given to him by the General Director.

***Part Three***
***Miscellaneous Provisions***

***14. Source of account***

Source of budget of the Agency shall be from the budget allocated to it by the City Government, its internal income, and donation.

***15. Books of account***

1. The Agency shall keep complete and accurate books of account.

2. Account the Agency shall audited by the Auditor General of the City Government or other person assigned by it.

***16. Inapplicable Laws***

Any proclamation, regulation, directive or customary practice which is inconsistent with this proclamation shall have no effect with respect to matters provided for the this Proclamation.

***17. Effective date***

This Proclamation shall enter into force as of the date of publication in Addis Negari Gazette.

**Addis Ababa**
**Done at 10th day of November 2009**

**Kuma Demeksa**
**Mayor of Addis Ababa City**